

# መካን ወላድ እናት ! !

እማማ : ወልደሽ: የመከንሽ፣
ይሁን :እድልሽ: ሰባራ እጣፈንታሽ፣
ያሳደግሽው ጡት ነካሽ : :
የባንዳ ልጅ ባንዳ ፣
ዛሬም አሳልፎ ሲሰጥሽ ላባዳ፣
መሬትሽን በገንዘብ ቸብችቦ፣
ስልቅጥ አርጎ በላሽ ሕጻናት አስርቦ፣
ለሕንድ ለጀርመን አሳልፍ የሰጠሽ፣
የነፃነትሽን ጮራ ከራስሽ ሊገፍሽ፣
የዶለተብሽ ያሳደግሽው፣
ከአብራክሽ የወጣው አራሙቻው : :
ያ ኣረማዊ ያ ዳተኛ፣
ያ ቅማንዠር ያ ዘረኛ፣
ሌት ተቀን ላንቺ አይተኛ : :
በትምክሕት ተወጥሮ ልቡን አሳብጦ፣
በተዳፈነ ረመጥ ውስጥ ተቁነጥንጦ፣
የሰላም አባት ለመሆን ሲዳዳው፣
ከቤቱ አልፎ የጎረቤቱን ችግር ሲያማስለው፣
መቼ ያበቃና መከራሽ ልጃችሽን ጠፍሮ አስሮብሽ፣
ሲቃሽን እያበዛ በየቀኑ ሞት እየሞትሽ፣
በጠራራ ፀሃይ በደም ጎርፍ እያታጠብሽ፣
አሳልፎ የሰጠሽ ያ ክፉ ጠላትሽ፣
ክብርሽን አዋርዶ ሰንደቅሽን ንቆ፣
የሞቶ ዓመት ዕድሜ የሰጠሽ ማነቆ : :
ያ ኣረማዊ ያ ዳተኛ፣
ያ ቅማንዠር ያ ዘረኛ፣
ሌት ተቀን ላንቺ አይተኛ : :
አርነቴን መረጥኩ ግፉ አንገብግቦኝ፣
ከሰር የሚነደው እሳቱ ለብለቦኝ፣
አሁን እነሳለሁ ነፃነቴን ብዬ፣
ወደኋላ አልልም ምኒልክ እምዬ፣
ወደኋላ አልልም ቴዎድሮስ ጀግናዬ : :

መይሳው ከምድረ ስዊድን

EthioLion.Com